ሐዋርያ ቅጽ 11፤ ቁጥር 5

መጋቢት-ሚያዚያ/1998 ዓ.ም

ርዕሰ አንቀፅ

# "መማር፥ መማር፥ አሁንም መማር"

ዐይኑን የከፈተና ልብ ያለ ሁሉ፥ በያንዳንዷ የጊዜ ቅጽበት ውስጥ አዳዲስ ነገሮችንና ክስተቶችን ያያል፥ ይገነዘባል ማለት ከተቻለ፥ መማር የማያቋርጥ ሂደት መሆኑን እንረዳለን። መማር ሲባልም፥ ፊደል ለይቶ ማንበብና መፃፍ፥ የሙያ ዘርፍ መርጦ መርቀቅና መፍጠር፥ ብቻውን ተቀንጽሎ አይገልጸውም። እውቀት በዚህ ብቻ የሚለካ ከሆነ፥ ማይምነት በሰው ልጆች ላይ ገና ድቅድቅ ጨለማውን፥ እንዳጠላ ነው ማለት ይቻላል። የእውቀት ምንጩ ማህበራዊና ተፈጥሯዊ መጋጠሚያ አለውና፥ እውቀትን ተቀባይና ገላጭ የሆነው የሰው ልጅ፥ ሁለቱንም ዘርፎች ሊማርባቸውና ሊጠቀምባቸው እኩል የሆነ መብት ስላለው፥ አካባቢውን ለመመርመርና፥ በጎና ክፉውን ለመለየት ሁልጊዜ ብቁ ነው። ሰፊው የእውቀት አድማስ ደግሞ ከዚህ የሚሰርጸውና እየዳበረ የሚሄደው ነው። ከማህበራዊውና ተፈጥሯዊው ባህርይ መስተጻምር፥ የሰው ልጅ በተቸረው ግንዛቤውና ምርምሩ፥ ረቂቅ የሆኑ ብዙ እውቀቶችን ያከማቻል። በዚህም የትናንት ልምዶቹንና ተመክሮዎቹን፥ ለዛሬው ህላዌ ክንውኑ ይጠቀምባቸዋል፤ የትናንቶቹን ኩነቶች ከዛሬዎቹ ድርጊቶች ጋር ደምሮ፥ ለነገው ገቢራዊ ጥቅም እያሰናዳ፥ አባል ከሆነባቸው ህብረተሰባዊና ተፈጥሯዊ የማያቋርጡ የለውጥ እንቅስቃሴዎች፥ አዳዲስ እውቀቶችን ለመገበየት፥ የከሸፉትን ለማረም ወይም ለመጣል፥ የተሻለባቸውን ለማዳበርና አመርቂ ውጤት ለማግኘት ዘወትር ይኳትናል።

በሀገራችን ማህበራዊ፥ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ የአስተሳሰብ ዘርፎች፥ ብዙዎች ዝንፈቶች የሚከሰቱት የነገሮችን ትሥሥርና አንደምታ በውል ካለመገንዘብ  የሚመጣ ይመስላል። አንዳንዶቻችን በግለሰብ ደረጃ፥ የድፍን ህብረተሰቡ ቅንጣቢ ውጤቶች መሆናችንን እንረሳና፥ ከብዙሃኑ በላይ የከበርንና ያወቅን እየመሰለን፥ የሕዝብን እድል ፋንታ ተክተን፥ ያለፍላጎቱና ጥያቄው ልንዘውረው እንሻለን። ይህ ራስን ከህብረተሰቡ የጋራ የእውቀት አድማስ በላይ የመሰየም አባዜ፥ እንዲቀጥል እድል ከተሰጠው ዳር ዳር የሚለው ወደ አጼነት፥ አምባገነናዊነት፥ ፈላጭ ቆራጭነትና በመጨረሻም ወደ አጥፍቶ ጠፊነት ነው።

በመረጥነው ጎዳናና፥ በተመቸን የሙያ መስክ፥ አንጻራዊ ክህሎት ማግኘት ምንጊዜም አስመስጋኝ ነው። የበቀልንበት ህብረተሰብ፥ ከእያንዳንዳችን በላይ ግዙፍ መሆኑንና፥ በውስጡ ያሉ አህዶችና ማህበረሰቦችም፥ በግልም ይሁን በጋራ፥ የዚህ ግዙፍ ሃይል ህዋሳቶች መሆናቸውን መረዳት አለመቻል ግን፥ አንዳችን ያለሌላችን አቅመቢስና ጎደሎ መሆናችንን ተገንዝበን አብሮ ለመኖርና ለማደግ አለመፈለግ ግን፥ አንዳችን ሌላችንን ምን ያህል ደካማ አድርገን ብንቆጥርም እንኳ፥ ችግሩን ተረድተን መፍትሄ ያልፈለግንለት ግንኙነት ሊያራምድ አለመቻሉን ካልተረዳን፥ አላዋቂ የሚያስብለንና የሚያስነቅፈን ነው። አንድ ሰው ወደ ማህበራዊ ኑሮ አገልግሎት፥ በተለይም ወደ ፖለቲካው ዓለም ሲገባ፥ ማንጸባረቅ ያለበት የህብረተሰቡን ፍላጎት፥ ምኞትና ህልም በውል መረዳቱንና ይህን እውን ለማድረግ መሣሪያ ሆኖ ለማገልገል መዘጋጀቱን እንጅ፥ ህብረተሰቡን ተክቶ ባለህልምና ምኞተኛ ለመሆን አይደለምና፥ ሁልጊዜ "እኔ ማን ነኝ፥ ከእነማንስ ጋር ነኝ" ማለት አስፈላጊ ይሆናል።

በፖለቲካው በኩል የሚታየው የትርምስ ወፍሬአልባነት፥ ምናልባት ብዙዎቻችንን ጥቂቶች ሁልጊዜ ያታሉናል፥ ወይንም ብዙዎቻችን ለጥቂቶች አድሃሪና አጎንባሽ የመሆን ባህል አጎልብተናል ካልተባለ በስተቀር፥ ብዙዎች ችግሮች የሚፈጠሩት፥ በአደራነት የተቀበልነውን የሕዝብ የበላይነትና የሀገር ጉዳይ ስንገድፍና፥ ለዘመናት የዳበረውን የህብረተሰብ ተመክሮና ልምድ ችላ ስንል ነው። የሕዝብ አልባሳት የሆነውን ጥበብ፥ በራሳችን ወርድና ስፋት ለክተን በመልበስ፥ ተቆንጥሮ በተኳኳለ ግላዊ መንፈስ ተሞልተን በመግዘፍ፥ የሕዝብን ግንዛቤና አቅም ዝቅ አድርገን የምንቆጥር ወገኖች መኖራችን ግልጽ ነው። በዚህ ደረጃ የምንገኝና እናውቃለን ባዮች፥ ለመማር ብዙ የሚቀረን ጉዳይ አለና፥ ተስፋ ለጣሉብንና ለሚያከብሩን፥ እንዲሁም ሃላፊነት ለሰጡን ሁሉ፥ ትሁትና አዳማጭ የመሆንን ጥበብ እንቅሰም።

ትምህርት ከራስ ድክመትና ጠንካራ ጎንም፥ ትምህርት ከሌሎች ክሳራና ትርፍም ያለማቋረጥ ይገበያል። በተለይ በማህበራዊ ጉዳዮችና በፖለቲካው መስክ ብቅ ብቅ ያሉ ወገኖች፥ ህጻናት ከእናት አባቶቻቸውና ከአካባቢያቸው ብዙውን ነገር እንደሚማሩት ሁሉ፥ ከአጭሩ የራሳቸው ተመክሮና፥ እንዲሁም ከነበሩና ካሉ ወገኖች፥ የሚገበዩት ተመክሮ ከፍተኛ ሲሆን፥ ከዚህ የትምህርት ገበታ የሚያገኙት ጠቃሚ እውቀትም የሚያስከፍላቸው ዋጋ አነስተኛ ነው። ከዚህ ቀደም የተገበየን ትምህርት ችላ ብለው፥ ወደፊት እየተሳሳትን እንማራለን ከተባለ ግን፥ ድፍረቱና ለመታረም ዝግጁነቱ በራሱ በጎ ቢሆንም፥ የሚጠይቀው ዋጋ ግን እጅግ ከፍተኛ መሆኑን እርግጠኛ ሆኖ መገንዘብ ያስፈልጋል።

በሌላ በኩል ደግሞ፥ በሕዝብ ስም ለሕዝብ ስንሰለፍ፥ ራሳችንን ለተተኪ ትውልድና ታሪክ ምሳሌ ለማድረግ መዘጋጀታችን ነውና፥ መጥፎ አዝማሚያንና ሥርዓት የጎደለውን አካሄድ፥ ቢቻል ለማስቀረት፥ አሊያ ለመቀነስ፥ ሁልጊዜ በመጣር መሣሪያነታችን ለሕዝብ መሆኑን ማስገንዘብ ይኖርብናል። ቦታና ጊዜ መርጠን በስህተቶቻችን ላይ ስንተራረምና ስንማማርም፥ ቂምን ቋጥረን ለመጎዳዳት እንዳይሆን ማሰብ፥ አስተያየቶቻችን ልዩ ትርጉም ተሰጧቸው መነታረኪያ እንዳይሆኑም መጠንቀቅ ይኖርብናል። ካለፉ ስህተቶች ለመታረም፥ በጎ ተመክሮዎችንም ለማጠናከርና አዳዲስ ልምዶችንም ለመገብየት ሁሉላችንም ያለማቋረጥ እንማር የምንለውም ለዚህ ነው።